# ለፀሐይ ባንክ አ.ማ ባለአክሲዮኖች በሙሉ

## የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባላት ጥቆማ ማስታወቂያ

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ ለዚሁ ዓላማ በተቋቋመ በአስመራጭ ኮሚቴ አማካይነት እንዲከናወን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ በባንኩ የባለአክስዮኖች 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ መመረጡ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት አስመራጭ ኮሚቴው የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባላትን ጥቆማ ከሰኔ 22 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ መስከረም 22 ቀን 2016 ዓ.ም ብቻ የሚቀበል ስለሆነ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SSB/71/2019 እና SSB/79/2021 ላይ የተዘረዘሩትንና የሚከተሉትን መሥፈርቶች የሚያሟሉ ዕጩ የቦርድ አባላትን እንድትጠቁሙ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

1. የባንኩ ባለአክሲዮን የሆነ፤
2. የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ፤
3. በሌላ የፋይናንስ ተቋም ውስጥ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ያልሆነ፤
4. በማንኛውም ባንክ ሠራተኛ ያልሆነ፤
5. ዕድሜው 30 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፤
6. የአስመራጭ ኮሚቴ አባል ያልሆነ፤
7. ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ እውቅና ካለው የትምህርት ተቋም ያለው፤
8. ሀቀኛ፣ ታማኝ፣ጠንቃቃ፣ ጠንካራ ሠራተኛ የሆነ እና መልካም ዝና ያለው፤
9. በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ በማጭበርበር፣ ዕምነት በማጉደል፣ ትክክለኛ ያልሆኑ የሒሳብ መግለጫዎች በማቅረብና በመሳሰሉት ተግባራት ተከሶ በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት የማያውቅ፤
10. እጩ ተጠቋሚዎች በቢዝነስ ማኔጅመንት፣በፋይናንስ፣ በአካውንቲንግ ፣በሕግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኦዲቲንግ፣ በኢንቨስትመንት ማኔጅመንት ወይም በንግድ ሥራ አመራር በተለይ በባንክ የሥራ ዘርፍ ልምድ ያላቸው እና የጾታ ስብጥራቸውም ተመጣጣኝ ቢሆን ይመረጣል፤
11. በራሱ ወይም በሚመራው ወይም ዳይሬክተር በሆነበት ድርጅት ላይ የመክሰር ክስ ያልቀረበበት ወይም የኪሳራ ውሣኔ ያልተሰጠበት እንዲሁም በኪሳራ ምክንያት ንብረቱ ለዕዳ ማቻቻያ ያልተወሠደበት፤
12. የባንክ ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት ንብረቱ በሐራጅ ያልተሸጠ፣ ተከሶ ያልተፈረደበት ወይም የሚመራው ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም የበላይ ኃላፊ የሆነበት ድርጅት ከገንዘብ ተቋማት የተበደረውን ገንዘብ ባለመክፈሉ ብድሩ ወደ ጤናማ ያልሆነ የብድር ደረጃ ያልዞረበት ወይም ያልገባበት፤
13. በቂ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ሰጥቶ ሒሳቡ ያልተዘጋበት፤

14. ታክስ ባለመክፈል ተከሶ የጥፋተኛነት ውሳኔ ያልተሰጠበት፣ እንዲሁም
15. ሌሎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና በሕግ የተገለጹ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>፡-

1. ከላይ በተዘረዘሩት መሥፈርቶች በወንድ ፆታ የተገለፀው በሙሉ ለሴትም ያገለግላል፡፡
2. ከፍተኛው የእጩ ተጠቋሚዎች ብዛት 24 ሲሆን፣ ከ24ቱ ተጠቋሚዎች 8ቱ በባንኩ ጠቅላላ የተፈረሙ አክስዮኖች ውስጥ 2% በታች የአክስዮን ድርሻ ባላቸው ባለአክስዮኖች ብቻ የሚጠቆሙ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹን 16 እጩዎች ሁሉም ባለአክስዮኖች ሊጠቁሙ ይችላሉ፡፡
3. ጥቆማውን ደብረዘይት መንገድ መዓዛ ደሳለኝ ህንፃ በሚገኘው የባንኩ ዋና መ/ቤት 1ኛ ፎቅ የዳይሬክተሮች ቦርድ  አስመራጭ ኮሚቴ ጽ/ቤት ወይም በባንኩ ቅርንጫፎች በሙሉ ማድረግ ይቻላል፡፡
4. ጥቆማ የሚደረግበትን ቅጽ ከባንኩ ዋና መ/ቤት 1ኛ ፎቅ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ጽ/ቤት፣ ከሁሉም የባንኩ ቅርንጫፎች፣ tsehaybank.com.et ከሆነው የባንኩ ድረ-ገጽ (ዌብሳይት) ወይም t.me/tsehaybanksc ከሆነው የባንኩ የቴሌግራም ቻናል ላይ በማውረድ ማግኘት ይቻላል፡፡
5. የባንኩ ባለአክስዮኖች የሞሉትን የጥቆማ ቅጽ ፈርመውበት ባንኩ ዋና መ/ቤት 1ኛ ፎቅ በሚገኘው የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ጽ/ቤት ወይም ወደ ባንኩ ቅርንጫፎች በመሄድ በጽ/ቤቱም ሆነ በባንኩ ቅርንጫፎች በተዘጋጀው የታሸገ ሳጥን ውስጥ በማስገባት ጥቆማቸውን ማከናወን ይችላሉ፡፡
6. ጠቋሚው ድርጅት ከሆነ የጥቆማ ቅፁ ላይ የድርጅቱ ህጋዊ ማህተም መደረግ ይኖርበታል፡፡
7. ተጠቋሚው ህጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ከሆነ መስፈርቶቹን የሚያሟላ ተቋሙን የሚወክል ግለሰብ ሊጠቆም ይገባል፡፡
8. ከነባር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትም መጠቆም ይቻላል፡፡
9. ጥቆማ ማቅረብ የሚቻለው እስከ መስከረም 22 ቀን 2016 ዓ.ም ከቀኑ 12፡00 ሰዓት ድረስ ብቻ ነው፡፡
10. ከመስከረም 22 ቀን 2016 ዓ.ም ከቀኑ 12፡00 ሰዓት በኋላ የሚቀርቡ ጥቆማዎች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን ከወዲሁ በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡
11. ለጥያቄና ተጨማሪ ማብራሪያ ባንኩ ዋና መ/ቤት 1ኛ ፎቅ በሚገኘው የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ፣ ወይም በስልክ ቁጥር 0114705354/0114704915 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡

**የፀሐይ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ**